# እንዴት እንታገስ

የደደቢቱ ተምች ፣ ሲገባ አዲሳባ
ሰላም መጣ እያለ ፣ ሲያስነፋ ጥሩምባ
ወያኔን ለሚተች ፣ እየሰጡ ጀርባ
ካውሮፓ አሜሪካ ፣ ተሰፈኛውም ገባ
የጎጠኛው ስርአት ፣ ጫንቃው እንደሰባ
ጥርሱን የነቀለው ፣ በተንኮል በደባ
ደብቆ የያዘውን ፣ ቀየረና ካባ
እሮጦ የገባውን ፣ ሲያረገው ሰለባ
ተጣድፎ መግባቱ ፣ ታውቆት እንዳልረባ
በሩጫ ፈርጥጦ ፣ ወጣት እንደገባ ።

ታሪክ ተደገመ ፣ ደግሞ በመደመር
በዲስኩር ጋጋታ ፣ ወሬ በመቆመር
በፅንፈኛ ዘውጌ ፣ በተሰላ ቀመር
የወያኔ አሰራር ፣ አንዱም ሳይቀየር
ምድረ ተቃዋሚን ፣ ባፍ ጄዶ መዘረር
እንዲህ ነው ጨዋታ ፣ ወንበር ሲመነዘር
የተደበቀ አመል ፣ ሲጋለጥ እያደር
በነ አቢቹ ሴራ፣ አይቀር መደናበር
ጨርቄን ማቄን ብሎ ፣ ድጋሚ መቋጠር
ሸሽት ወደ አውሮፓ ፣ መፈርጠጥ ከሃገር ።

በመናፍቅ መድረክ ፣ ባለው ተመክሮ
በንቶ ፈንቶ ዲስኩር ፣ ሁሉንም አስክሮ
ያዳራሹን መንጋ ፣ ዳንኪራ አስጨፍሮ
ሃሌሉያ እያያለ ፣ መድረክ ላይ ዘርሮ
ልምዱን ያካበተው ፣ ፓስተሩ መሪያችን
አልሸሹም ዞር አሉ ፣ ሾመን በላያችን
አይነኬ ሆነው ፣ ዛሬ ንጉሳችን
እያፈናቀሉን ፣ ከገዛ አገራችን
በግፍ በጭካኔ ፣ ሲገሉ ሺዎችን
እፁብ ድንቅ ያሰኛል ፣ ፍርሃት ዝምታችን
እንዴት ያለው ጀግና ፣ ይተቻል ጌቶችን ።

ንጉስ አይከሰስ ፣ ሰማይ አይታረስ
የኛ ፖለቲካ ፣ ዘወትር ማነከስ
አንጃ እየፈጠሩ ፣ ድርጅትን ማፍረስ
ሲሻሩ ማንጓጠጥ ፣ ሲሾሙ ማወደስ
ጎጀው ባናትህ ላይ ፣ እየጋየ ሲጨስ
አትንኩ ንጉሱን ፣ አገር ሲናድ ሲፈርስ
የማይሞከር ነው ፣ ባለጊዜን መክሰስ
እንደ ጣዖት ማምለክ ፣ አጎብድዶ ማጉረስ
ወንበር የከዳው ለት ፣ ትችትና መውቀስ
አድር ባዩን ታዲያ ፣ እንዴት እንታገስ ።

ታዛቢው

February 12, 2019